Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Health

President's Malaria Initiative

# ጋዜጣዊ መግለጫ

## የኢትዮጵያ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ የአሜሪካ ፕሬዚዳንት የወባ መከላከያ መርሀ ግብርና ዩኒሴፍ ወባን ለማጥፋት በህብረት እየሠሩ ነው፡፡

በአጎበሮች፣ በመድሀኒቶች እንዲሁም በወባ በሽታ ምርመራ አገልግሎቶች; ለከፍተኛ የወባ አደጋ በተጋለጡ አካባቢዎች የሚኖሩ 22 ሚሊዮን ኢትዮጵያውያን ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡

ታህሳስ 10 ቀን 2005 ዓ.ም፣ አዲስ አበባ- በዛሬው ዕለት በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ በአሜሪካን ፕሬዚዳንት የወባ መከላከያ መርሀ ግብርና በዩኒሴፍ መካከል በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር መስሪያ ቤት ውስጥ ለአምስት ዓመታት የሚቆይ የ 100 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር የዕርዳታ ስምምነት ተፈርሟል፡፡

የጤና ጥበቃ ሚኒስትሩ ዶክተር ከሰተብርሃን አድማሱ፣ በኢትዮጵያ የአሜሪካን አምባሳደር ዶናልድ ኢ ቡዝ፣ እንዲሁም በኢትዮጵ የዩኒሴፍ ተጠሪ ዶክተር ፒተር ሰላማ በኢትዮጵያ ውስጥ በተለይም በኦሮሚያ ክልል በወባ በእጅጉ ተጠቂ ለሆኑ አካባቢዎች ወባን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚደረገውን ጥረት በእጥፍ የሚያሳድገውን ይህንን ስምምነት ተፈራርመዋል፡፡

ይህ ከአሜሪካ መንግስት፣ በዩኒሴፍ በኩል የሚሰጠው ዕርዳታ፣ ኢትዮጵያ የነደፈችውን ብሔራዊ ወባን የመከላከል የመቆጣጠርና የማስወገድ ስልት (2004-2008) ለማጠናከር ከመርዳቱም በላይ፣ ህይወት ሊታደግ የሚችል ፍቱን የወባ መድሐኒቶችና የወባ መመርመሪያ ቁሳቁሶችን በማቅረብ፣ በፀረ ተባይ ኬሚካሎች የተነከሩ አጎበሮችን ለማሰራጨት ጭምር ያግዛል፡፡ በተጨማሪም ይህ ዕርዳታ ኢትዮጵያ የተያያዘችውን ህበረተሰብ አቀፍ የተቀናጀ የሕጻናት ዋና ዋና በሽታዎች ህክምናና ቁጥጥር ስልትን ከግቡ ለማድረስ ይረዳል፡፡ እነዚህም አገልግሎቶች በጤና ኤክስቴንሽን መርሀ ግብር አማካይነት የሚቀርቡ ናቸው፡፡

የዚህ ስምምነት ዋና፣ ዋና ተግባራት፣ ለወባ በሽታ ተጋላጭ በሆኑ አካባቢዎች የሚኖሩ 22 ሚሊዮን ሕዝብ ለመታደግ የሚያስችሉ 11 ሚሊዮን ፀረ ተባይ ኬሚካሎች የተነከሩ አጎበሮች ገዝቶ ማቅረብን፣ ለ 12.6 ሚሊዮን ሰዎች ህክምና ሊውል የሚችል የወባ መድሐኒት ገዝቶ ማቅረብን፣ 16.5 ሚሊዮን ፈጣን የወባ መመርመሪያ ቁሳቁሶችና ሌሎች ፀረ ወባ መድሐኒቶች ገዝቶ ማቅረብን ያካትታሉ፡፡ በተጨማሪም፣ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ የአሜሪካን ፕሬዚዳንት የወባ መከላከያ መርሀ ግብርና፣ ዩኒሴፍ በመተባበር

የወባ መድሐኒቶችንና ሌሎች ግብዓቶችን ዕቅድ በማሻሻሉ ተግባር ላይ በጋራ መስራታቸውን ይቀጥላሉ፡፡

የእርዳታው ስምምነት ከተፈረመ በኂላም የጤና ጥበቃ ሚኒስትሩ ዶክተር ከሰተብርሃን አድማሱ፤ "ካልታከሙ በስተቀር ወባ የሚገድል በሽታ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ በተጨማሪም ሊወገድ የሚችል ህመምን በማስከተል ምርታማነትና የኢኮኖሚ ዕድገትን በመቀነስ፤ በአገሪቱ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ላይ ማነቆ ይሆናል፡፡፡ ወባን መከላከል ወሳኝ ተግባር እንደመሆኑ አጋሮቻችን ማለትም፤ የአሜሪካን መንግስትና ዩኒሴፍ በአገራችን ከወባ ጋር በተያያዘ የሚደርሰውን በሽታና ሞት ለመቀነስ በመርዳታቸው ከልብ እናመሰግናለን" በማለት የዕርዳታውን ጠቀሜታ በአንክሮ ገልጸዋል፡፡

በኢትዮጵያ የአሜሪካ አምባሳደር የሆኑት ዶናልድ ኢ ቡዝ በበኩላቸው፡- "በአሜሪካ ፕሬዚደንት የወባ መከላከያ መርሀ ግብር ተጠቃሚ በመሆን ኢትዮጵያ ተቀዳሚዋ አገር ናት፤ ኢትዮጵያ ወባን በመከላከል ረገድ አመርቂ ለውጥ በማስገኘት ማንም ሕጻን ፤ ማንም ቤተሰብ፤ ማንኛውም ህብረተሰብ በዚህ አቅምን በሚያዳክምና በሚገድል በሽታ እንዳይጠቃ የማድረግ ብሎም የመግታት አቅም እንዳላት በተግባር አሳይታለች፡፡ ወባ ከአምስት ዓመት ዕድሜ በታች ላሉ ሕጻናት ሞት ዋነኛ መንስዔ ከሆኑት በሽታዎች አንዱ ነው፡፡ እናም ማንኛውም ሕጻን አምስተኛ ዓመትና ከዚያም በላይ የልደት በዓሉን የማክበር ዕድል ሊኖረው ይገባል" ብለዋል፡፡

በኢትዮጵያ የዩኒሰፍ ተጠሪ ዶክተር ፒተር ሰላማም በበኩላቸው፡- "ኢትዮጵያ በጤናው ዘርፍ ከፍተኛ ለውጥ አስመዝግባለች፡፡ በመሆኑም የሕጻናትን ሞት የመከላከል የምዕተ ዓመቱን የልማት ግብ ለመምታት በሚያስችላት ትክክለኛ ጎዳና ላይ ትገኛለች፡፡ ይህንን ዕርዳታ በማግኘቷና በኢትዮጵያ መንግስት፤ በአሜሪካ መንግስትና እንዲሁም በዩኒሴፍ መካከል ያለው ትብብር ተዳምሮ ኢትዮጵያ በእናቶችና ሕጻናት ጤና ረገድ የምታስመዘግበው ውጤት ለሌሎች አገሮች ተምሳሌት እንደሚያደርጋት አልጠራጠርም" ብለዋል፡፡

**ለበለጠ መረጃ የሚከተለውን ይጠቀሙ፡-**

አህመድ ኢማኖ፤ በፌዴራል የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የሕዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት ዲሬክተር- ቀጥታ ስልክ- +251 115 518031 ሞባይል- + 251-911388946
ኢሜይል ahmed_emano@yahoo.com

ወይዘሮ ወሰን ሙላቱ፤ የኮሙኒኬሽን ኦፊሰር፤ ዩኒሴፍ ኢትዮጵያ
ቀጥታ ስልክ፤ + 251-11-5184028 ሞባይል +251 911-308483 ኢሜይል፤
wmulatu@unicef.org